የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

፴፫ኛ ዓመት ቁጥር ፺፬
አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

33th Year No. 94
Addis Ababa 8th March, 2025

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፻፹፬/፳፻፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ**

ገጽ ……………………………………………፫ሺ፰፻፸፪

**CONTENT**

**REGULATION No.184/2024**

**ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO DIRECT AND REGULATE THE NON-FORMAL TRADE ACTIVITY**

Page… … … … … … … … … … … … …3872

**ደንብ ቁጥር ፻፹፬/፳፻፲፯**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ**

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ በመደበኛው የንግድ ሥርዓት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑን በመገንዘብ ይህንን ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ በሥርዓት ካልተመራ በከተማ ውበትና ገጽታ፣ በከተማ ጽዳት፣ በትራፊክ ፍሰትና እንቅስቃሴ፣ በኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት እና በከተማዋ ሰላምና ፀጥታ አጠባበቅ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል በመሆኑ፤

**REGULATION No.184/2025**

**ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REGULATION TO DIRECT AND REGULATE THE NON-FORMAL TRADE ACTIVITY**

**WHWREAS, WHWREAS,** it has become necessary to fix non-formal street trade is becoming more and more prevalent in Addis Ababa city is recognizing that it is negatively impacting the formal commercial system;

**WHWREAS,** it has been found necessary to urban beauty and scenery; urban cleanup, traffic flow and activity, and the prevalence of smuggling and the fact that it causes great hardship in the city's peace and security if non-formal street trade is not regulated by order;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘትና የሚያስከትላቸውን ችግሮች መቅረፍ የሚቻለው ዘርፉ ህጋዊ ሆኖ በሥርዓት ሲመራ በመሆኑና ዘርፉን ሥርዓት በማስያዝ በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣው ደንብ ቁጥር ፹፰/፪ሺ፱ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ መተካት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፭ አንቀፅ ፺፬ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

WHWREAS, it has become necessary to keep people in the sector engaged into a formal business system and it is possible to find the economic benefits of non-formal street trade and to address the problems it causes, as the sector has been legalized and run orderly;

WHEREAS, it has been found necessary to Regulations No. 88/2017, which had previously been in force to direct and systemize non-formal business, made it more in line with the current situation, requiring replacement;

NOW, THEREFORE, this regulation is issued by the Cabinet of Addis Ababa City Government in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፹፬/፪ሺ፲፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. **"የንግድ ሕግ"** ማለት የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ነው፤

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Regulation to Direct and Regulate the Non-formal Trade Activity Regulation No. 184/2025".

### 2. Definition

In this regulation, unless the context or the phrase provides otherwise:

1. "**Government**" means the Addis Ababa City Government;
2. "**Commercial Code**" means the commercial code of Ethiopia;

፫. **"አዋጅ"** ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ነው፤

፬. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ ነው፤

፭. **"ጽሕፈት ቤት"** ማለት እንደአግባቡ የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤

፮. **"ጎዳና"** ማለት ዋና መንገድ፣ መጋቢ መንገድ፣ ቀለበት መንገድ፣ አደባባይ፣ የእግረኛ መንገድ፣ የመንገድ አካፋይ፣ የመንገድ ዳርቻ ሲሆን ክፍት ቦታዎችን ይጨምራል፤

፯. **"መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ"** ማለት በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም ቋሚ የንግድ ቤት ወይም ቦታ ሳይኖረው በዚህ ደንብ መሠረት በተፈቀደ ቦታ እና ቀናት በጎዳና ላይ እስከ ብር ፪፻ሺ ብር /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በሚገመት አነስተኛ ካፒታል ሸቀጦች እና አገልግሎቶችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለሽያጭ በማቅረብ የሚሠራ የንግድ ሥራ ዓይነት ነው፤

፰. **"መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ"** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት በተፈቀደ ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚያካሂድ ሰው ነው፤

፱. **"እሁድ ገበያ"** ማለት በተመረጡ ጎዳናዎች ወይም ክፍት ቦታዎች አምራቾች፣ አርሶ አደሮች፣ ጅምላ ነጋዴዎች እና በኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ማህበራት ቅዳሜና እሁድ ምርት፣ ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ግብይት የሚያካሂዱበት ቦታ ነው፤

3. "**Proclamation**" means the commercial registration and business licensing proclamation;

4. "**Bureau**" means the trade bureau of the Addis Ababa city government;

5. "**Office**" means the trade office of a sub-city or woreda administration, depending on the appropriate circumstances;

6. "**Street**" means main street; feeder road, ring road, square; sidewalk; road divider, roadside which adds open spaces when it is open;

7. "**Non-Formal Street Trade**" means a type of business that operates by offering goods and services to the consumer society for sale in small capital goods and services on the street at an approved location and days under this regulation, without registering on a commercial register and issuing a business license or having a permanent business house or place, at an estimated cost of 200,000.00 /two hundred thousand/ Birr;

8. "**Non-Formal Street Trader**" means someone who conducts a street business in an approved place; day and time according to this regulation;

9. "**Sunday Market**" means a place where producers, farmers, wholesalers, and enterprise-organized associations in selected streets or open spaces can deny weekend produce, merchandise, or service marketing;

፲. **"መዝገብ"** ማለት በመደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚመዘገቡበት በቢሮው የሚዘጋጅ ዋና መዝገብ ነው፤

፲፩. **"ቋሚ የመገበያ ቦታ"** ማለት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል ተለይቶ ለንግድ የተመደበ ወይም የተዘጋጀ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ቀን፣ ሰዓት እና የሥራ ዘርፍ ወይም መሰል ፕሮግራም የወጣለትና በዚሁ መሠረት ሳይቋረጥ ቦታው ለልማት ወይም ለሌላ አገልግሎት እስኪፈለግ ድረስ በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፪. **"ጊዜያዊ የመገበያ ቦታ"** ማለት ለንግድ ሥራ ቀንና ሰዓት ፕሮግራም ያልተያዘለት የንግድ ዘርፍ ወጥቶለት ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጁ ጎዳናዎች በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፫. **"መደበኛ ያልሆነ ጽዳት"** ማለት የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በመደበኛነት በዕቅድ ከሚያፀዳቸው የተለያዩ ቦታዎችና ጎዳናዎች በተለየ ሁኔታ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ የሚካሄድባቸውን ሥፍራዎች በሙሉ ሥራውን ተከትሎ ማፅዳቱ በተወሰነለት ዕለትና ሠዓት ከተከናወነ በኋላ በልዩ ሁኔታ የሚካሄድ የጽዳት ሥራ ነው፤

፲፬. **"ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ"** ማለት በደረት ላይ የሚንጠለጠል ሆኖ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለሚሠራ ነጋዴ በበጀት ዓመቱ የተሰጠ ወይም የታደሰ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚታደስበት ጊዜ ያላለፈበት ፈቃድ ወይም መታወቂያ ወይም መለያ ነው፤

10. "**Record**" means a main record prepared by the bureau so as to register those individuals who are involving in the non-formal trade activity;

11. "**Permanent Market Place**" means a place allocated or prepared for the trade and in which a program is scheduled for the date, time and business type of the non-formal trade activity and such continues as per the thereof until the site is needed for development that for the purposes of the enactment of this regulation;

12. "**Temporary Market Place**" means a place where the non-formal trade activity is being carried out, having set the business type, on the roads and roundabouts which are prepared for such activity where the day and time fir the trade activity is not programmed;

13. "**Non-Formal Sanitation**" means a sanitation activity especially carried out in all the places where non-formal trade activity is held followed by its happening as per the specified day and time of the thereof by the sanitation administration agency, in a special condition, out of its regular and planned cleaning of the various places, avenues, roads and roundabouts;

14. "**A License that Hanging from the Chest**" is a license or identification or label issued or renewed during the fiscal year for a tradesman who operates a non-formal street trade while hanging from the chest, or has not expired for renewal under the Sub Article (3) of Article 14 of this regulation.

፲፭. **"አስተዳደራዊ እርምጃ"** ማለት ይህን ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ በሚገኝ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ በቢሮው ወይም በክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አማካይነት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ፈቃድ እስከ መሠረዝ የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

፲፮. **"ግብረ ኃይል"** ማለት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲካሄድ በበላይነት የሚመራ፣ እና ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ አካል ነው፤

፲፯. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፰. በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፬. <u>ዓላማ</u>

የዚህ ደንብ ዓላማ፡-

፩. መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚመራበትን ሥርዓት በመዘርጋት ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ እንዲሆን ማስቻል፤

፪. በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በመፍታትና በቂ ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ ወደ መደበኛ ንግድ ሥርዓት እንዲገቡ ማስቻል ነው፡፡

15. "**Administrative Measure**" means a measure taken by, as may be necessary, the Bureau or Office of the sub-city or woreda on the non-formal trader who disobeys this regulation and other relevant directives from giving a verbal warning to revocation of the permit;

16. "**Task Force**" is the body that oversees, and provides monitoring support for, the operation of an non-formal street trade system in a manner that is in place;

17. "**Person**" means a natural or juridical person;

18. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This regulation shall be applicable on any individual who is involving in the non-formal trade activity within the region of the Addis Ababa city government.

## 4. <u>Objective</u>

The objective of this regulation is:

1. By establishing a system through which non-formal street trade could be run, enabling it to be helpful for the economy and social movement;
2. It is to enable them to enter the formal trade system next by resolving the problems seen in the sector and providing adequate support.

## ክፍል ሁለት
## ስለ ምዝገባ እና ፈቃድ አሰጣጥ

**፭. መዝገብ ስለማደራጀት**

፩. መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት መዝገብ በዚህ ደንብ ይደራጃል፤

፪. ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማናቸውንም ሰው ይመዘግባል፡፡

**፮. ስለመመዝገብ**

፩. ማንኛውም ሰው በመዝገብ ሳይመዘገብ በየትኛውም ቦታ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤

፪. የእሁድ ገበያ በመባል የሚታወቁት እና የትራፊክ ፍሰት የማይበዛባቸውን ቦታዎች ለጊዜው በመዝጋት በሳምንት ቅዳሜና እሁድ መደበኛ ባልሆነ ጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚሰማራ ሰው በዚህ ደንብ መሰረት መመዝገብ አለበት፤

፫. የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍና የገበያውን ዋጋ ለማረጋጋት በእሁድ ገበያ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለተጠቃሚው በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ከቢሮው ወይም ከጽህፈት ቤቶች ጋር በትስስር የንግድ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች በዚህ ደንብ መሰረት መመዝገብ አለባቸው፤

፬. ማንኛውም ሰው በመዝገብ የሚመዘገበው በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፭. ማንኛውም ሰው በመዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

## PART TWO
## REGSITRATION AND ISSUANCE OF PERMIT

**5. Record Organization**

1. A record, which is used to register any individual who is involving in the non-formal street trade activity, shall be organized by this regulation;
2. The Bureau shall register any individual who is engaged in the non-formal street trade activity within the city government according to this regulation.

**6. To be Registered**

1. Any individual shall not be permitted to involve in a non-formal trade activity in any place within the region of the city government without being registered on the record;
2. A person, who engages in business on an non-formal street trade on a weekend, known as a Sunday market and temporarily closing the areas where traffic is not frequent, must register under this regulation;
3. In order to shape the cost of living and stabilize the market price, people who do business with the Bureau or offices in a tailor's business must register under this regulation to provide agricultural and industrial products to the consumer at an affordable price on the Sunday market;
4. Any individual shall be registered on the record in the office of the woreda near where he works;
5. Any individual shall be registered only once on the record.

**፯. <u>በመዝገብ ስለሚገቡ ጉዳዮች</u>**

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ መዝገብ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

፩. የነጋዴው ስም ከነአያት፣

፪. ዜግነት፣

፫. የመኖሪያ አድራሻ፣

፬. የጎዳና ላይ ንግዱ የሚካሄድበትን አድራሻ፣

፭. የንግዱ የሥራ ዓይነት ወይም መስክ፡፡

**፰. <u>የምዝገባ መስፈርት</u>**

በመደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ አመልካች የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

፩. በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው ፪ (ሁለት) ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

፪. በከተማ አስተዳደሩ ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ዲጂታል መታወቂያ፣

፫. ከግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

፬. ዕድሜው ፲፰ ዓመት የሞላው መሆኑን ማረጋገጫ ፣

፭. በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ ወይም ሌላ ማንኛውም ሥራ ላይ ያልተሠማራ እና ሥራ አጥ መሆኑን በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የጽሁፍ ማስረጃ፣

፮. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) የተደነገጉ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በእሁድ ገበያ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማቅረብ ከቢሮው ወይም ከጽ/ቤት ጋር ትስስር የፈጸመ ከሆነ የትስስር ሰነዱን በማቅረብ ብቻ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

**7. <u>Issues that go on Record</u>**

A non-formal record of street trade needs to contain the following information:

1. The merchant's full name;
2. Citizenship;
3. Residential address;
4. Address to the street trade's run;
5. The trade's type of work or sector.

**8. <u>Registration Requirement</u>**

An applicant wishing to engage in non-formal street trade must submit the following documents:

1. Two (4*4) photographs of the applicant which are taken within six months period;
2. Digital ID that ensures that he is resident in city government;
3. Tax Payer Identification Number (TIN) given by the office of the tax collector;
4. Proof of being 18 years old;
5. Written evidence from the Woreda administrative office in which he resides in the city government that he is not engaged in regular trade or any other job and is unemployed;
6. In this Article, although there are Provisions from Sub Articles (1) to (5), under Sub Article (3) of Article 6 of this regulation, if it has made a tie to the Bureau or office for the provision of agricultural and industrial products on the Sunday market, it can only be registered by providing the binding document.

**፱. ስለፈቃድ አሰጣጥ**

፩. ማንኛውም መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቢሮው ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በማያያዝ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፤

፪. ማንኛውም ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የወረዳው ጽሕፈት ቤት አግባብ ባለው ደንብ መሠረት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግዱ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ይሰጠዋል፤

፫. ቢሮው ለምዝገባ አገልግሎት የሚውሉ ወጥ ቅፆችን ያዘጋጃል፤ ለወረዳ ጽሕፈት ቤት ይልካል፤

፬. ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ደረጃውን የጠበቀ እና በቀላሉ ሊዘጋጅ የማይችል መሆን ይኖርበታል፡፡

**፲. የምዝገባ መረጃዎችን ስለማስተላለፍ**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዝገባ መረጃዎችን በየዕለቱ ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል፤ የክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት በሚቀጥለው ቀን ለቢሮው ያስተላልፋል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽህፈት ቤት የምዝገባ መረጃዎችን ለክትትል እንዲያመች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

፫. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተላለፈለትን የምዝገባ መረጃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መዝግቦ ይይዛል፤ እንደአስፈላጊነቱ በሚዘጋጅ ሶፍትዌር ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ላይ ይመዘግባል፡፡

**9. Registration Application and Giving Decision**

1. Any individual who wants to involve in a non-formal trade activity should fill the application form prepared by the bureau together with attaching the evidences stated under Article 7 of this regulation and submit it to the Woreda Office before starting the business;
2. If the submitted application for registration is accepted, the Woreda Office shall register and give a permit that will be hanging from the merchant's chest after receiving the specified payment according to Article 19 (1) of this regulation;
3. The Bureau shall prepare similar forms used for the registration purpose; make send it to the Woreda Office;
4. A permit hanging from the chest should be standardized and not readily prepared.

**10. Transferring Registration Information**

1. The Woreda Office that carried out the registration based on this regulation shall transfer the registration information daily to the Sub-City using a form prepared for such a case. The Office of the Sub-City shall also transfer the thereof to the Bureau on the second day.
2. The Woreda Office that has made registration as protected as provided by Sub Article (1) of this Article must notify the relevant stakeholders in writing to facilitate the follow upping of registration information;
3. The Bureau maintains a record of the registration information passed under Sub Article (1) of this Article under Sub Article (2) of Article 5 of this Regulation, which records on the modern management of information by software being developed as required.

## ፲፩. እውቅና ስለመስጠት

በዚህ ደንብ መሠረት ተመዝግቦ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ገበያ ለማረጋጋት በእሁድ ገበያ ላይ ትስስር የተፈጠረለት እና በተፈቀደ ቦታ ላይ የሚሠራ ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

## ፲፪. ስለምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ

፩. ማንኛውም ሰው መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራውን ለማካሄድ ከተመዘገበበት እና ከተመደበበት የሥራ ቦታ አካባቢ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አካባቢ ለመለወጥ ሲፈልግ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፫) እና አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት በቅድሚያ ያደረገውን ምዝገባ ማስረዝና ከወረዳው ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት መመለስ አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ምዝገባው የተሰረዘና ፈቃዱን የመለሰ የጎዳና ላይ ነጋዴ መሸኛ ወረቀት በመውሰድ ወደ መረጠው አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት በመሄድ መሸኛውን አቅርቦ መመዝገብ ይችላል፤

፫. ማንኛውም ሰው ተመዝግቦ የሚሰራውን የንግድ መስክ ዓይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ከፈለገ የተመዘገበበት ወረዳ ጽሕፈት ቤት በመቅረብ በቢሮው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሚሠራውን የንግድ መስክ ዓይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይችላል፤

፬. የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ስለመቅረቡ እና ተቀባይነት ስለማግኘቱ የወረዳው ጽሕፈት ቤት ማረጋገጫ መስጠት እና ተቀባይነት ያገኘበትን ቀን፣ ስለምዝገባው ለውጥ ወይም ማሻሻያ በዝርዝር በመግለጽ ለአመልካቹ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 11. Giving Recognition

Any person who engaged in non-formal trade activity that was registered as per this regulation and was given a permit which is hanging from the chest or engaged in a Sunday market to stabilize a market, and who worked in an approved place shall be recognized legally to carry out a small business activity in accordance with this regulation.

## 12. Registration Change or Improvement

1. If anyone wishes to change from their registered and assigned workplace environment to another workplace environment in order to conduct their non-formal street trade, he must cancel his prior registration under Article 6 Sub Article (3) and Article 9 Sub Article (2) of this Regulation, and return to the Woreda Office a permit hanging from the chest issued from the Woreda Office;
2. According to Sub Article (1) of this Article, a street trader who has had his registration revoked and has returned his permit can take a shipping paper and go to a Woreda Office in his chosen area to make the delivery and register the carry;
3. Any person shall appear at the office of the Woreda that he has registered and fill a form prepared by the Bureau if he wants to change or improve the already registered business type being carried out to another one;
4. The Office of the Woreda shall give assurance for the submittal of the registration change or improvement and acceptance of the thereof; and notify the date of acceptance and registration change or improvement to the applicant and relevant stakeholders in writing in detail. The submitted registration change or improvement shall not be considered as replaced or upgraded unless the written assurance is given.

**፲፫. ደረት ላይ ስለሚንጠለጠል ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የተሰጠ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ በዚህ ደንብ መሰረት ካልተሠረዘ እና በየዓመቱ የታደሰ ከሆነ የጸና ይሆናል፡

፪. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የበጀት ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት ፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ድረስ ግብር እስከፋይ መስሪያ ቤት ግብራቸውን ወስኖ እንዲከፍሉ ያደርጋል፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በበጀት አመቱ ከሐምሌ ፩ ጀምሮ እስከ ታህሳስ ፴ ድረስ ከግብር እስከፋይ መስሪያ ቤት ክሊራንስ በማቅረብ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ በየአመቱ ፈቃዱን ለሰጠው ወረዳ ጽህፈት ቤት ቀርቦ መታደስ አለበት፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በበጀት አመቱ ፈቃዱን ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ክፍያ እጥፍ በመክፈል ፈቃዱን ማሳደስ ይችላል፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ፈቃዱን ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ ሰው ከመዝገብ ይሰረዛል፡ ተመዝጋቢው የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ መመለስ አለበት፡ ሳይመልስ ቢቀር በእጁ እንዳለ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡

**13. Effective Date and Renewal of Permit Hanging from the Chest**

1. Under the Sub Article (2) of Article 9 of this Regulation, a permit hanging from a given chest shall be upheld if it is not revoked under this regulation and renewed annually;
2. Anyone engaged in street trade will have their taxes fixed and charged from July 1, until August 30, within the 2-month period following the end of the fiscal year;
3. Under Sub Article (2) of this Article, a renewal of the permit must be filed and renewed with the Woreda Office which granted the permit each year, paying the appropriate fee by providing clearances from the pay Taxes Office from July 1 of the fiscal year until December 30;
4. Under Sub Article (3) of this Article, a non-formal trader who did not renew his permit or identification during the fiscal year could renew his permit by paying double the fee, thus renewing his permit;
5. According to Sub Article (4) of this Article, a person who has not renewed his permit or identification will be disqualified from the record; the subscriber must return a permit hanging from the chest given to him; if he does not answer, he is considered to be erased as if he were in his possession.

**፲፬. <u>ምትክ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

፩. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ምዝገባ ያደረገ ማንኛውም ሰው የተሰጠው ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት እንደሆነ ቀደም ሲል ለሰጠው የወረዳ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ በማመልከት ምትክ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፤

፪. ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃዱ የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ይመልሳል፤

፫. የወረዳው ጽህፈት ቤት ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጠፋው ወይም ለተበላሸው ፈቃድ ወይም መታወቂያ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፡፡

**፲፭. <u>የተመዘገበና ተንጠልጣይ ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ</u>**

ማንኛውም በዚህ ደንብ መሰረት የተመዘገበና ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

**፩. መብቶች**

ሀ) በመዝገብ ያስመዘገበውን እና የተፈቀደለትን የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ማካሄድ፤ ፤

ለ) የተሰጠው ፈቃድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ምትክ መውሰድ፤

ሐ) የሚነግድበትን የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የሚነግድበት ቦታ ወይም አካባቢ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት አሳውቆ የመለወጥ፣ የማሻሻል፤

መ) የመነገጃ አካባቢውን ወይም የሚነግድበትን የሥራ መስክ መሰረት በማድረግ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በማኅበር የመደራጀት፤

**14. <u>Issuance of Replacement Permit Hanging from the Chest</u>**

1. Anyone who has registered a street trade can obtain a permit in exchange for applying in writing to the Woreda Office that had previously granted it that a permit hanging from the chest given was lost or defaced;
2. Anyone whose permit hanging from the chest was defaced would return the derelict when he asked for a replacement;
3. The Woreda Office issues a permit or ID in lieu of charging the appropriate service fee for the permit or ID lost or damaged upon application.

**15. <u>Rights and Obligations of a Person who is Registered and Granted the Permit Hanging from the Chest</u>**

**Any person** registered under this regulation and granted to permit hanging from the chest:

1. **<u>Rights</u>**
   a) Conducting the street trade that records and is authorized; taking a permit;
   b) Taking a replacement if the permit given to was lost or damaged;
   c) Notified the Woreda Office of the business sector of the street that trades and the place or area where it trades, and provided for conversion, improvement, development;
   d) Of organizing by association under appropriate law based on the area of conduct or the area of work in which it trades;

## ፪. ግዴታዎች እና ክልከላዎች

ሀ) የወረዳው ጽህፈት ቤት በፈቀደለትና በመደበው ቦታ፣ ዕለት፣ ሰዓት፣ እና የሥራ ዘርፍ ላይ ብቻ መሥራት አለበት፣

ለ) መደበኛ ላልሆነ ንግድ ሥራ የሚይዛቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች፣ የገዛበትን ህጋዊ ደረሠኝ ማቅረብ አለበት፣

ሐ) ለሸማቹና ለተጠቃሚው ተገቢውን ክብር መስጠት አለበት፣

መ) ከመዝጋቢው አካል የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ አንገቱ ላይ በማጥለቅ በግልጽ እንዲታይ ማድረግ፣

ሠ) በመዝጋቢው አካል መረጃ ሲጠየቅ መረጃውን ወዲያው መስጠት አለበት፣

ረ) የጎዳና ላይ ንግድ ሥራውን ሲጨርስ አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት አለበት፣

ሰ) የአካባቢውን ንጽህና፣ ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ አለበት፣

ሸ) ባልተፈቀደ ቦታ መነገድና የትራፊክ እንቅስቃሴ ማወክ የለበትም፡፡

ቀ) በውክልና መመዝገብ የተከለከለ ነው፣

በ) ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚይዛቸው ዕቃዎችን ጥራት፣ መጠን፣ ይዘት መለወጥ ወይም ማጉደል፣ ሸማቹን እና ተጠቃሚውን ማጉላላት የለበትም፣

ተ) የተሳሳቱ ወይም ተመሳስለው የተሰሩ ምርቶችን መሸጥ የለበትም፣

ቸ) የብቃት ማረጋገጫ ወይም መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች መያዝ የለበትም፣

ኀ) የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ እንዳይበላሽ በጥንቃቄ መያዝ፣ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

## 2. Obligation and Restrictions

a) The Woreda Office must only work on the location, date, time, and employment that it permits and assigns;

b) Must supply the industrial products it holds for the operation of a non-standard business, the legal receipt of which it bought;

c) Showing proper respect for consumers and users;

d) To make a putting permit on the chest which was given by the registerer around the neck and make it clearly visible while on duty;

e) Provide information promptly up on the request of the registerer;

f) Properly clean the place when finishing the non-formal trade activity;

g) Keep the hygiene, peace and security of the surroundings;

h) Have the obligation not to sell at unpermitted places and not to disturb the traffic flow;

i) Registration by proxy is prohibited;

j) The quality, quantity, content of the goods it holds for street trade should not be changed or disrupt, nor should it the consumer focus and user;

k) Not selling false or fake products;

l) Not possessing products that demand competency assurance or criterion;

m) Hold carefully to prevent the putting on a given chest from being to avoid spoiling; he should not hand it over to another person.

**፲፮. ስለ አገልግሎት ክፍያ**

ቢሮው መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ምዝገባ እና ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ወይም መታወቂያ ለመስጠት ወይም ለማደስ እና ለተያያዥ አገልግሎቶች የሚጠየቁ የአገልግሎት ክፍያዎችን እያጠና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**፲፯. ከመዝገብ ስለመሰረዝ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ**

፩. በመደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ይሰረዛል፦

ሀ) የንግድ ሥራውን ካቆመ፣

ለ) ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ፣

ሐ) ሐሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ መመዝገቡ ከተረጋገጠ፣

መ) ከተፈቀደለትና በመታወቂያው ላይ ከተገለጸው ቦታ ወይም ቀን ወይም ሰዓት ወይም የጎዳና ላይ ንግድ የሥራ ዘርፍ ውጪ ወይም ባልተፈቀደ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ከተገኘ፣

ሠ) ቢሮው ወይም የወረዳ ጽሕፈት ቤቱ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክል እና በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፣

ረ) የሸማቹን የጤናና የጽዳት አጠባበቅ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የንግድ ዕቃውን ጥራት ወይም አይነት ደረጃ ካጓደለ ወይም ሌላ ሕገ ወጥ ተግባር ከፈጸመ ወይም በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎች ወይም የራሱ ያልሆነውን በአዋጁ መሠረት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ነጋዴ ዕቃ ይዞ ከተገኘ፣

**16. Service Payment**

The Bureau provides informal access to the registration of street trade and to the relevant authority for issuing or renewing a permit or identification hanging from the chest and studying service fees required for associated services, which it applies when permitted.

**17. Revocation from a Record and Taking Administrative Measure**

1. Any individual who is involved in a non-formal trade activity shall be revoked from the record due to the following reasons:
   a) Termination of the trade activity;
   b) Death;
   c) Being found registered using fraud information or document;
   d) If found working in contrary to the permitted and described place, date, time or the non-formal trade activity on the ID or involving in a trade activity that is not allowed;
   e) If fails to correctly and timely submit information required by the Bureau or the Woreda Office;
   f) If fails to meet the quality or type or standards of health and hygiene safety, environmental protection of the consumer and the commodity or service; or committing other illegal activity or possessing contraband goods or other goods owned by a trader involving in a formal trade activity according to the Proclamation;

ሰ) ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ካልታደሰ፡

ሸ) ሸማቹን በማታለል ወይም በማሳሳት ተግባር ላይ ከተገኘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ይህን ደንብ የጣሰ እንደሆነ፡

፪. ቢሮው መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ በሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር ይህንን ደንብ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የጎዳና ላይ ንግድ የሚያከናውን ማንኛውም የተመዘገበና ፈቃድ ያለው ሰው ሲያገኝ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡

፫. ማንኛውም የጎዳና ላይ ነጋዴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱ ጥፋቶችን መፈጸሙ ሲረጋገጥ፡-

ሀ) ቢሮው ወይም የወረዳ ጽህፈት ቤት አጥፊውን መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ ከመዝገብ በመሰረዝ ስለመሰረዙ በጽሁፍ ያስታውቀዋል፤

ለ) ፈቃዱ የተሰረዘበት የጎዳና ላይ ነጋዴ ቢሮው ወይም የወረዳው ጽህፈት ቤት የሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ተመላሽ ማድረግ አለበት፤

ሐ) የንግድ ዕቃዎቹንና የመገልገያ ዕቃዎቹን በማንሳት የጎዳና ላይ ንግድ ሲሰራበት የነበረውን የመነገጃ ቦታ ይለቃል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ለጎዳና ላይ ንግድ የሚፈቀዱ የሥራ መስኮች፤ የመነገጃ ቦታዎች እና ወደ መደበኛ ንግድ ሥራ ስለማሸጋገር

### ፲፰. ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ስለሚፈቀዱ የሥራ መስኮች

፩. መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው የሚሰራው የንግድ ሥራ ዓይነት፤ የሥራ መስክ ወይም የሥራ ዘርፍ ዝርዝር በህግ የተፈቀደ መሆን ይገባዋል፡

g) If the permit hanging from the chest is not renewed according to Sub Article( 3)of Article 14 of this Regulation;

h) If found in any act of cheating or misleading the consumer or violates this Regulation in any other condition.

2. Bureau is warned when any registered and licensed person who does street trade in some way obtains it, and he contradicts this Regulation through his support and inspection of the non-formal systemization of street trade;

3. When it is proved that any street trader committed faults relating to Sub Article (1) of this Article:

a) The Bureau or Woreda Office announces in writing about the abolition of the perpetrator by revoking an informal street trader from a record.

b) A street trader whose permit has been revoked must return a permit hanging from the chest that the Bureau or Woreda Office has issued;

c) Removes its trade goods and utilities and releases the place where the street trade used to operate.

## PART THREE

## WORK FIELDS PERMITTED FOR STREET TRADE, PLACE OF MARKET AND TRANSITION TO A REGULAR TRADE

### 18. Work Fields Permitted for Street Trade

1. A person engaged in non-formal street trade is a type of business that works, a list of a work field or career is to be authorized by law;

፪. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ ሰዉ ለመሥራት የሚፈቀዱ የንግድ ሥራ ዓይነቶች ወይም መስኮች ቢሮው በየጊዜው እያጠና በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡

፫. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ፮ እና ፲፫ መሰረት መመዝገብና ፈቃድ ማውጣት የማያስፈልጋቸውን ጥቃቅን መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ አይነቶች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡

፬. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰዉ የሚሰራው የንግድ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና መስፈርት የማያስፈልገዉ የንግድ ሥራ ዓይነት መሆን አለበት፡፡

**፲፱. <u>የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለማካሄድ ስለሚፈቀድባቸው ቦታዎችና የማከናወኛ መገልገያዎችን ስለመወሰን</u>**

፩. የጎዳና ላይ ንግድ ለመሥራት የመነገጃ ቦታ ሊሰጥ የሚቻለው ከሚከተሉት ምድቦች በአንዱ ይሆናል፡-

ሀ) በቋሚ የመነገጃ ቦታ፣

ለ) በጊዜያዊ የመነገጃ ቦታ፣

ሐ) የቅዳሜና የእሁድ ገበያ፣

፪. የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ መሥራት የሚቻለው የከተማውን ዋና ዋና መንገዶች፣ የከተማውን ውበት በማይነካ ብሎም ደህንነት በጠበቀ መልኩ በሚመለከታቸዉ አካላት በጥንቃቄ ተለይተው በሚፈቀዱ ጎዳናዎች ላይ በግብረ-ኃይሉ ይሁንታ ሲያገኝ ብቻ ይሆናል፣

፫. መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ የተፈቀዱ ጎዳናዎችን በሚመለከት ቢሮው የመለያ ምልክቶችን ያስቀምጣል ወይም ይተክላል ወይም እንዲከለሉ ያደርጋል፣

2. Subject to the Provision of Sub Article (1) of this Article, the types or fields of business permitted to operate for a person engaged in non-formal street trades are determined by the Directives that the Bureau is periodically studying;

3. The Bureau may, under this Articles 6 and 13, determine, by Directives, the types of minor non-formal street trade that do not need to register and issue permits;

4. A business that is engaged in street trade must be a type of business that does not require the certification and requirement of professional qualifications.

**19. <u>Determination of Areas where Street Trade is Permitted to Conduct Business and Performing Facilities</u>**

1. A place to do street trade can be provided by one of the following categories:

   a) At a permanent market place;

   b) At a temporary market place;

   c) Saturday and Sunday market.

2. Street trade can only be done when it receives the approval of the task force on streets that are carefully identified by the parties concerned, in such a way as to ensure the City's main streets; and in a way that does not affect the City's beauty, nor is it safe;

3. In the case of irregular streets approved for street trade, the Bureau will place signage or plant or have them blocked;

፬. መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚፈቀዱ ቦታዎች ከትራፊክ እንቅስቃሴ እና ፍሰት ማሳለጥ አንፃር፣ ከመንገድ ሊኖራቸው የሚገባውን ርቀት ፣ ለሸማቾች የሚኖራቸውን አመችነት እና ቅርበት፣ የመደበኛ ነጋዴዎችን ገበያ አለአግባብ እንዳይሻማ ከመከላከል አንፃር እና የመሳሰሉትን መስፈርቶች ወይም ስታንዳርድ ይሆናል፤

፭. ቢሮው የንግድ ሥራውን ዓይነትና ባህሪይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ማከናወኛ የሚውሉ ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ተገጣጣሚ የከተማውን ውበት ማስጠበቅ የሚችሉ እና አቅምን ያገናዘቡ መገልገያዎች ዓይነትና ዲዛይናቸውን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

## ፳. <u>ወደ መደበኛ የንግድ ሥራ ሽግግር ስለ ማድረግ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሰረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሥራ ላይ ከተሰማራበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፪ (ሁለት) ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የሀብት መጠን ብር ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የደረሰ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት መሸጋገር አለበት፤

፪. ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት ስለሚሸጋገርበት ሁኔታ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፳፩. <u>ድጋፍና ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

፩. የወረዳው ጽህፈት ቤት የቁጥጥር ባለሙያ የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው ግዴታዎችን በትክክል መወጣቱንና በዚህ ደንብ መሠረት ሥራው መከናወኑን ለማረጋገጥ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፤

4. Informally permitted areas for street trade, in terms of traffic movement and streamlining; the distance they must have from the road; the convenience and proximity they have to consumers; in terms of preventing the undue market of regular traders, and so on, will be a requirement or standard;

5. Considering the type and character of the business, the Bureau also develops or develops the type and design of modern portable prefabricated city beauties capable of maintaining commercial operation for the street, and capacitive facilities.

## 20. <u>Making the Transition to a Regular Trade</u>

1. Under this Regulation, anyone engaged in non-formal trade must be transitioned a formal trade system from the time of their employment to the age of 2 (two) years when the total amount of wealth reached 200,000 (two hundred thousand) Birr;

2. It will be determined by the Bureau's Directive on the transfer to a formal business system.

## 21. <u>Providing Support and Inspection</u>

1. Inspectors of the Woreda shall inspect and provide support so as to ensure whether the registered individual who was given the permit or ID hanging from the chest is fulfilling his obligation properly and the business is being carried out as per this Regulation or not;

፪. በቢሮው ወይም በጽሕፈት ቤቱ ለቁጥጥር ሥራ የሚሰማራ የቁጥጥር ሠራተኛ የተሰጠውን የመስሪያ ቤት መታወቂያ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራው ሰው በቅድሚያ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ ግብረ ኃይል መቋቋም፣ ድጋፍ፣ ክትትል እና የባለድርሻ አካላት ሚና

### ፳፪. ግብረ ኃይል ስለማቋቋም

፩. መደበኛ ያልሆኑ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የሚደረገውን ተግባር ከግብ ለማድረስ የሚሰሩ አስተግባሪ አካላትን በበላይነት አቀናጅቶ የሚመራ ግብረ ኃይል በማዕከል፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪. የማዕከሉ ግብረ ኃይሉ ተጠሪነት ለከተማው ከንቲባ ይሆናል፡፡

### ፳፫. የግብረ ኃይሉ አባላት አሰያየም

፩. የግብረ ኃይል አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) የከተማው ምክትል ከንቲባ ........ ሰብሳቢ፣

ለ) የንግድ ቢሮ ኃላፊ ........... አባልና ፀሐፊ፣

ሐ) የሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ ........ አባል፣

መ) የሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ .................................................. አባል

ሠ) የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ .................................................. አባል፣

ረ) የሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ............................................ አባል፣

ሰ) የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ............... አባል፣

ሸ) የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር.................................. አባል፣

ቀ) የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ .................................... አባል፣

በ) የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ............................. አባል፣

2. Any inspection Officer of the Bureau or Office that carries out the inspection should show his work place ID first to the individual who is involving in a non-formal trade activity.

## PART FOUR
## ESTABLISHING TASKFORCE, SUPPORT AND INSPECTION AND CONTRIBUTION OF STAKEHOLDERS

### 22. Establishing A Taskforce

1. A task force at city, sub-city and wereda level was set up under this Regulation, which oversaw and guided the taskforces working to achieve the task of the non-formal street trade;
2. The task force at City level will be accountable to the Mayor of Addis Ababa City.

### 23. Naming of the Taskforce Members

1. Task Force Members will be:
   a) Deputy Mayor of the City Government........................Chairperson;
   b) Head of the Trade Office...............Member and Secretary;
   c) Head of Labor and Skill Bureau.................................. Member;
   d) Head of Peace and Security Administration Bureau ……. Member;
   e) Head of the Bureau of Land Development and Administration …………………………………Member;
   f) Head of Women, Children and Social Affairs Bureau;…………….. Member;
   g) Head of the Revenue Bureau.................................. Member;
   h) Head of the Traffic Management Authority.............................. Member;
   i) Manager of Code Enforcement Authority ………………………Member;
   j) Head of the Sanitary Management Agency...................................Member;

ተ) የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ................................ አባል፤

ቸ) የምግብና መደሃኒት ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ................................ አባል፤

፪. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአባላቱ ቁጥር በከንቲባ ሊጨምር ይችላል፡፡

## ፳፬. የግብረ ኃይሉ ተግባርና ኃላፊነት

ግብረ ኃይሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. የዚህን ደንብ አፈጻጸምና አተገባበር በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፪. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባል፤

፫. በባለድርሻ አካላት መካከል ውጤታማ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፬. የጎዳና ላይ ንግድ የሚፈቀዱ ቦታዎችን አስመልክቶ በቢሮው ወይም በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅተው የሚቀርቡ መስፈርቶች እና ስታንዳርዶች ላይ ተወያይቶ ያጸድቃል፤

፭. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ እንዲውሉ በሚመለከታቸው አካላት ተለይተውና ተዘጋጅተው በሚቀርቡ የመነገጃ ቦታዎች ላይ ተወያይቶ ይወስናል፤

፮. የደንቡ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት አፈጻጸም አስመልክቶ ወቅታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል፤ የአፈጻጸም ድክመት ባሳዩት ላይ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፯. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ነጋዴዎች ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት የሚሸጋገሩበትን አቅጣጫ ወይም ስትራቴጂ ይቀይሳል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፤ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

k) Addis Ababa City Police Commission Commissioner........................Member;

l) b) Head of the Food and Drug Authority............................ Member.

2. The number of Members may be increased by mayor when necessary.

## 24. Duty and Responsibility of the Task force

The task force will have the following duty and responsibilities:

1. It oversees, follows up, controls the implementation of this Regulation;
2. It makes policy recommendations in relation to street trade;
3. It follows up and confirms the existence of effective coordination between stakeholders;
4. Discusses and approves requirements and standards of street trade that are prepared and proposed by the Bureau or relevant authorities regarding permitted areas;
5. It discusses and decides on places of trade that are identified and prepared by the parties concerned for the use of the street trade;
6. It requires the executive bodies of the Regulation to submit a timely report on the performance of the duties and responsibilities assigned to them by this Regulation, reviews their performance, and provides to the Mayor to be held accountable for those who have demonstrated a weakness in performance;
7. It would change the direction or strategy by which the merchants engaged in street trade would be transitioned to a formal trade system, and it would monitor its implementation, and take corrective action;

፰. ለዚህ ደንብ ማስፈጸሚያ በቢሮው የሚወጡ ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ይመክራል፤

፱. አስተግባሪ አስፈጻሚ አካላት ለግብረ ኃይሉ ውሳኔ በሚያቀርቧቸው ሌሎች ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲. የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና የውስጥ ደንብ ያወጣል፤

፲፩. የዚህን ደንብ ማሻሻያ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡

**፳፭. ግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት**

፩. ግብረ ኃይሉን በሰብሳቢነት ይመራል፤ የስብሰባ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ግብረ ኃይሉን ይወክላል፤

፪. የግብረ ኃይሉ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥሪው ለግብረ ኃይሉ አባላት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

፫. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፬. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎችና ሰነዶች በግብረ ኃይሉ ፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

**፳፮. የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎችና የስብሰባ ሥነ-ስርዓት**

፩. ግብረ ኃይሉ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፪. ከግማሽ በላይ የሆኑ የግብረ ኃይሉ አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፤

8. It advises on draft Directives issued by the Bureau for the enforcement of this Regulation;

9. It makes decisions on other strategic issues that the coordinator executive bodies makes decisions for the taskforce;

10. It establishes its own meeting procedure and internal rule;

11. It makes proposals for the reform of this Regulation.

**25. Task Force Chairperson's Duty and Responsibility**

1. He leads the task force as a chairperson, where he makes a call for a meeting pass, and represents the task force in communications with third parties;
2. The taskforce's meeting will be held in a timely manner, where it will find it necessary to call an emergency meeting so that the call can be turned over to Members of the taskforces;
3. Ensures the taskforce decisions are implemented;
4. Follows-up whether decisions and documents of the taskforce are well organized through the Secretary of the taskforce.

**26. Meetings and Meeting Procedures of the Taskforce**

1. The taskforce meets once every month, however, when it finds it necessary, it may call a meeting at any time;
2. The quorum is considered complete when more than half of the task force members are present;

፫. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም የተሰጠው ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ ያልፋል፤

፬. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎችንና ሰነዶች በፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፤

፭. ሰብሳቢው እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ አካላትን ግብረ ኃይሉ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፤

፮. ግብረ ኃይሉ የራሱን የስብሰባና የአሰራር ሥነ-ስርዓት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

**፳፯. <u>የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አስተግባሪ ግብረ ኃይል ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩. የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አስተግባሪ ግብር ኃይሉ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፬ ለማዕከሉ አስተግባሪ ግብረ ኃይል የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት በአስተዳደር እርከኑ ተፈጻሚ ያደርጋል፤

፪. ሌሎች ከማዕከሉ ወይም ከክፍለ ከተማው አስተግባሪ ግብረ ኃይል የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፳፰. <u>የክፍለ ከተማው እና የወረዳው አስተግባሪ ግብረ-ኃይል አባላት</u>**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ የተዘረዘሩ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ተቋማት ኃላፊዎች የክፍለ ከተማ አስተግባሪ ግብረ ኃይል አባላት ይሆናሉ፤

፪. የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳው ግብረ ኃይሉ ተጠሪነት ለክፍለ ከተማው ወይም ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

3. The decision of the taskforce is passed by majority vote, in the event of an equal vote, the Chairman has casting vote;
4. Follows-up the taskforce decisions and documents are well organized through a secretary;
5. The Chairperson may also have other relevant parties participate in the taskforce meeting as an evidence, as required;
6. The taskforce may determine its own meeting and operational procedure with Directive.

**27. <u>Duties and Responsibilities of the Executing Task Force at Sub-city and Wereda Level</u>**

1. The sub-city and Wereda executing task force shall cause the implementation of the duties and responsibilities of the executing task force at city level that are specified under Article 24 of this Regulation at the respective administrative stratum;
2. Carry out other duties given by the executing task force at city or sub-City level.

**28. <u>Members of the Sub-City and Wereda Task Force</u>**

1. The Heads of Sub City Administrative Agencies listed in Article 23 of this Regulation shall be Members of the Sub City and Sub-City task force;
2. The task force at sub-city or Wereda level will be accountable to the Chief Executive of the Sub City.

## ፳፱. <u>የደንቡ አስፈፃሚ አካላት ሚና</u>

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ይህን ደንብ ለማስፈፀም እንደየድርሻቸው የሚከተለው ሚና ይኖራቸዋል፡-

፩. **<u>የንግድ ቢሮ ሚና</u>**

ሀ) በመደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ ሰዎችን እና የመገበያ ቦታዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይለያል፤

ለ) የተለዩና መስፈርቱን የሚያሟሉ መደበኛ ያልሆኑ የጎዳና ላይ ነጋዴዎችን ይመዘግባል፤

ሐ) በጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በማህበር እንዲደራጁ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሰራል፤ ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤

መ) መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በገበያ ማረጋጋት እና አጠቃላይ ለከተማዉ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረዉን አስተዋፅኦ ያጠናል ወይም እንዲጠና ያደርጋል፤

ሠ) በዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የመገበያ ቦታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ረ) ለመገበያ ቦታ የሚከፈል የኪራይ መጠን ይወስናል፤

ሰ) መደበኛ ካልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

## 29. <u>Contribution of the Executive Bodies of the Regulation</u>

The following stated executive bodies of the City Government will have the following role depending on their stake in implementing this Regulation:

1. **Contribution of the Trade Bureau**

a) Identifies the people who may be involved in non-formal street trade and places of information in coordination with stakeholders;

b) Records non-formal street traders who are identified and meet the criteria;

c) Performs the work of creating awareness for people involved in street trade to be organized into associations, it coordinates, and supports;

d) It studies or makes studies of the contribution of an non-formal street trade in entrepreneurship made by market stabilization and overall development to the City's economy;

e) Makes it possible for women engaged in the field and people with disabilities to benefit from a priority place of market;

f) Determines the amount of rent to be paid for the place of market;

g) Provides training that allows them to transition from a non-formal street trade to a more formal trade system.

**፪. የሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ሚና**

ሀ) መደበኛ ያልሆነ ወይም የእሁድ ገበያ ንግድ ሥራ በሚከናወኑባቸው ጎዳናዎች፣ አደባባዮችን እና ክፍት ቦታዎች ላይ ህግና ሥርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ለ) የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እና ከሚመለከታቸው አስተግባሪ ግብረ ኃይል አባላት ጋር በመቀናጀት ወንጀል፣ የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የማስተባበር ሥራዎችን ይሰራል፣ ተፈጽሞ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

**፫. የሥራና ክህሎት ቢሮ ሚና**

ሀ) መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ወደ መደበኛ ንግድ ለመሸጋገር የሚያስችላቸውን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ለ) በማህበር ተደራጅተው መደበኛ ባልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ የመነገጃ ቦታ ወይም ሌሎች ከሥራ እድል ፈጠራ ጋር የተያያዙ ድጋፎችን ለሚጠይቁ የመነገጃ ቦታ ማግኘት የሚችሉበትን ያመቻቻል፣

**፬. የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ሚና**

ሀ) የመነገጃ ቦታ ዝግጅት በተመለከተ የከተማዉ ፕላን በሚፈቅደዉ የመሬት አጠቃቀምና አግባብ ያላቸዉ ህጎችን መሰረት በማድረግ በዚህ ደንብ መሰረት በጎዳና ላይ ንግድ ለሚሰማሩ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታዎችን በማጥናት ይለያል፣ የመነገጃ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ከቢሮዉ ጋር በመሆን መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች የሥራ ቦታ በጥንቃቄ ይፈቅዳል፣

2. **Contribution of Peace and security Administration Bureau**

a) It follows up and inspects the observance of law and order and the maintenance of public peace and security in streets trade, squares, Sunday market trade and open spaces where in non-formal or street market trade is conducted;

b) carry out activities to prevent crimes, code violations and related illegal activities by enhancing the participation of the community and collaborating with the task force members ; cause the taking of legal measures when such is committed;

3. **Role of Labor and Skill Bureau**

a) Shall facilitates conditions that women, people with disabilities, and citizens with special needs engaged in informal street vending to receive attention in technical and vocational training that will enable them to transition to formal trading;

b) Facilitate access to a workstations or who request other support related to job creation; for those who are engaged in informal street trading organized by micro-enterprises

4. **Contribution of Bureau of Land Development and Administration**

a) Concerning the preparation of a business place, study and identify a permanent and temporary business place for individuals who are going to be involved in the non-formal trade activity as per this Regulation based on the land utilization and ratified laws set by the City's plan, prepare and assign business places; permit business places for those who are going to engage in the business together with the trade Bureau.;

ለ) የሚያዘጋጃቸው ቋሚና ጊዜያዊ የመንገድ ቦታዎች ከይገባኛል ጥያቄ ነፃ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡

**፭. <u>የሴቶች፣ ሕጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሚና</u>**

ሀ) መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች መብት፣ ጥቅምና ደህንነት የሚያስከብሩ መሆናቸውን ይከታተላል፡

ለ) መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መሥራት፣

**፮. <u>የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ሚና</u>**

ሀ) ከከተማው የትራንስፖርት እና የትራፊክ እንቅስቃሴ ጋር አጣጥሞ መደበኛ ያልሆነ ወይም የእሁድ ገበያ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራዎች የሚካሄድባቸውን መንገዶች የመለየት ሥራ ይሰራል፡ ምልክት ያደርጋል፡ የለያቸውን ለቢሮው ያሳውቃል፡ ከትራፊክ እንቅስቃሴ ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፡

ለ) መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ እንዲካሄድባቸው በተፈቀዱ መንገዶች ላይ የአደጋ መከላከያ ምልክቶች ያስቀምጣል፡ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን ይመድባል፡

**፯. <u>የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ሚና</u>**

ሀ) መደበኛ ያልሆነ ወይም የእሁድ ገበያ ንግድ ሥራ በሚካሄድባቸው ጎዳናዎች፣ አደባባዮችን እና ክፍት ቦታዎች ላይ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች የተመዘገቡና ፍቃድ ያላቸው መሆኑን ይከታተላል፡ ይቆጣጠራል፡ ያልተመዘገበ እና ያለ ፈቃድ ሲሰራ የተገኘ ሰው ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡

b) Ensures that the permanent and temporary places of order that it prepares are free of claim.

5. **<u>Role of Women, Children, and Social Affairs Bureau</u>**

a) Follow up whether informal street trading activities respect the rights benefits and safety of women and people with disabilities;

b) Work in collaboration with relevant organs to ensure that women and persons with disabilities to actively participate in the economic activities of the informal street trading as well as benefit from the thereof;

6. **<u>Contribution of Traffic Management Authority</u>**

a) Identify places for carrying out the nonformal trade activity in line with the transport and traffic flow of the City; it marks, informs the Bureau of those who identify them, and exempt them from traffic activities;

b) Places signs of risk protection on roads that are allowed to carry out non-formal business; it assigns supervisory professionals.

7. **<u>Contribution of the Code Enforcement Authority</u>**

a) It follows up and inspects whether people who performs street trade are registered and permitted in the streets where non-formal or Sunday market trade is conducted; in squares and open spaces; it takes legal action against a person who is unregistered and found to be operating without a permit;

ለ) ባልተፈቀዱ መንገዶች፣ አደባባዮች ፣ ክፍት ቦታዎች ላይ የጎዳና ላይ ንግድ እንዳይካሄድ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

ሐ) በተፈቀዱ መንገዶች፣ አደባባዮች እና ክፍት ቦታዎች ላይ እንዲነግዱ በቢሮው የተፈቀደላቸው ሰዎች በተፈቀደለት ቀን፣ ሰዓት፣ ቦታና በተፈቀደለት የሥራ ዘርፍ መሰማራቱን፣ የከተማውን የውበት ደረጃ በጠበቀ መልኩ እየተካሄደ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለቢሮው ያሳውቃል፣

**፰. <u>የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ሚና</u>**

ሀ) ኤጀንሲው ልዩ የጽዳት ፕሮግራም በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት የጎዳና ላይ ንግድ የሚካሄድባቸውን መንገዶችና አካባቢዎች መደበኛ የጽዳት የሥራ ጊዜውን ሳይጠብቅ ጽዳት ያካሂዳል፣

ለ) እንደአስፈላጊነቱ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችን ያስቀምጣል፣ በወቅቱ ያነሳል፣

**፱. <u>የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን</u>**

ሀ) የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ይህን ደንብ ለማስፈጸም ቁጥጥር ሲያደርግ የፖሊስ ድጋፍ በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ድጋፍ ያደርጋል፣

ለ) የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ያለውን ሰላምና ፀጥታ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስከብራል፣

**፲. <u>የምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን</u>**

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት በጎዳና ላይ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦችን አስመልክቶ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከጤንነት ጋር በተያያዘ ቁጥጥር ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል።

b) It follows up and inspects the street trade in squares, open spaces in unauthorized ways; it takes legal action;

c) It follows-up, inspects and notifies the Bureau for legal action to be taken people allowed by the Bureau whether it is being carried out in keeping with the City's aesthetic standards; to trade in permitted roads; squares and open spaces on the date of approval; time; place and participation in permitted work.

8. **<u>Contribution of Sanitary Management Agency</u>**

a) The agency shall clean the roads and its surroundings in which the non-formal trade activity is carried out, as per this Regulation, by setting special cleaning program without following the regular cleaning program;

b) Will deposit landfill pools as required, lifting them at the time.

9. **<u>Addis Ababa City Police Commission</u>**

a) When a Code Enforcing Authority has control to implement this Regulation, it provides police support in cases that are required;

b) It follows-up, inspects, and maintains the peace and security of the place for carrying out the non-formal trade activity is carried out.

10. **<u>Food and Drug Authority</u>**

The authority, under this Regulation, exercises inspection in relation to health under the relevant law regarding food for sale on the streets; it takes legal action when necessary or makes it possible to take it.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴. ስለተጠያቂነት**

ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ሲገኝ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፴፩. በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ**

በዚህ ደንብ መሠረት በክፍለ ከተማው ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ማንኛውም ሰው፡-

፩. እርምጃው ከተወሰደበት ወይም ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በአስተዳደራዊ እርከን ደረጃ ተዋረዱን በመጠበቅ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት፣ ለክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም ለቢሮው አቤቱታ በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፤

፪. አቤቱታ የቀረበለት አካል በ፲ (አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔውን በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሣወቅ አለበት፡፡

**፴፪. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፴፫. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ከግብረ ኃይሉ ጋር በመመካከር ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴፬. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣው ደንብ ቁጥር ፹፰/፳፻፲፩ ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**30. Liability**

Any person who violates the Provisions of this Regulation shall be held liable according to the relevant laws.

**31. Submitting Grievance on the Administrative Measure**

In accordance with this Regulation, any person to whom an administrative measure has been taken:

1. May submit his grievance in writing hierarchically to the day that the administrative measure was announced by the Bureau of the Sub-City or Woreda;
2. The body that accepted the petition shall give its response to the complainant within ten (10) working days in writing.

**32. Duty to Cooperate**

Any person shall be duty bound to cooperate in executing of this Regulation.

**33. The Power to Issue Directives**

The Bureau may issue a Directive in consultation with the taskforce for the execution of this Regulation.

**34. Repealed and Inapplicable Laws**

1. Addis Ababa City Government Regulation to Direct and Regulate the Non-formal Trade Activity Regulation No. 88/2017 is here by repealed by this Regulation;

፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፴፭. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከየካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አዳነች አበቤ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. Any Regulation, Directive or Customary Practice of the City Government, which is inconsistent with this Regulation, shall not be applicable on matters covered under this regulation.

**35. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of March 8, 2025

**Done at Addis Ababa, this 8th day of March, 2025.**

**Adanech Abiebie**
**Mayor of Addis Ababa City**